መዝገብ ቁጥር 233682

የካቲት 29 ቀን 2015ዓም

ዳኞች ፡-ብርሃኑ አመነዉ

በእውቀት በላይ

ቀነአ ቂጣታ

ሌሊሴ ደሳለኝ

ኑረዲን ከድር

አመልካቾች፡-አቶ ተክላይ ካህሳይ - ጠበቃ በላይ መሸሻ -ቀረቡ

ተጠሪ፡ ዋልታ ሜዳያና ኮሚኒኬሽን ኮርፖሬት -ተወካይ ፍሬው በፍቃዱ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

***ፍርድ***

የሰበር አቤቱታዉ ሊቀርብ የቻለዉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 89684 ላይ በ28/08/2014 ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 277353 ላይ በ18/12/2014 ዓ.ም የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ በማሻሻል የወሰነዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል እንዲታረምላቸዉ ነሐሴ 25 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ በማቅረባቸዉ ነዉ፡፡

ጉዳዩ የስራ ክርክርን የሚመለከት ስሆን ክርክሩ በጀመረበት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡የጉዳዩ መነሻ በአመልካች በኩል መጋቢት 12 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ ያቀረቡት ክስ ስሆን ይዘቱም፡በተጠሪ ተቋም ዉስጥ ከሚያዚያ 21 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ዉሉ እስከ ተቋረጠበት ታህሳስ 11 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ ለ 6 አመታት ከ 8 ወራት ያህል በጥበቃ የስራ መደብ ላይ በወር 4,681.00(አራት ሺህ ስድስት መቶ ሰማንያ አንድ ብር ) እየተከፈላቸዉ ስሰሩ መቆየታቸዉን፡፡ ይሁን እንጂ መንግስት ባወጣዉ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ጋር ተያይዞ ምክንያቱን ባላወቁበት ሁኔታ ጥቅምት 24 ቀን 2014 ዓ.ም ተይዘዉ በተለያዩ ማቆያ ቤቶች በኋላም ልዩ ስሙ አባ ሳሙኤል የተባለ ቦታ ታስሬዉ እስከ ጥር 8 ቀን 2014 መቆየታቸዉን፡፡በእስር ላይ ባሉ ጊዜ እስከ ህዳር ወር 2014 ዓ.ም ያለዉ ደሞዝ ተጠሪ የከፈላቸዉ መሆኑን ከእስር ከተፈቱ ከጥር 9 ቀን 2014 ዓ.ም ወደ ተጠሪ መስሪያ ቤት በመሄድ ወደ ስራ እንዲመልሱኝ ያልተካፈላቸዉ ደሞዝ እንዲከፈላቸዉ ስጠይቁ ሲያመላልሱኝ ከቆዩ በኋላ ታህሳስ 11/2014 ዓ.ም የስራ ዉል መቋረጡን የሚገልጽ ደብዳቤ መጋቢት 2 ቀን 2014 ዓ.ም አስፈርመዉ እንደሰጡዋቸዉ ተጠሪ ያላአግባብ የስራ ዉሌን ያቋረጠ በመሆኑ ከታህሳስ ወር 2014 ዓ.ም ክሱ እስከ ቀረበ ድረስ ያልተከፈላቸዉ የ4 ወር ዉዙፍ ደሞዝ እንዲከፈለኝ ወደ ስራዬ እንዲመልሱኝ ይህ የሚታለፊ ከሆነ ደግሞ የካሳ ክፍያ፤የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ፤የስንብት ክፍያ ፤የ2012 እና የ2013 ዓ.ም ያልተጠቀሙ የ45 ቀን የአመት ዕረፍት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ ፤ክፍያ ለዘገየበት የ3 ወር ደሞዝ እንዲከፈላቸዉ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተጠሪ በ26/07/2014 ዓ/ም በተጻፈ መልስ ያቀረቡ ስሆን ይዘቱም፤ አመልካች በተጠሪ ድርጅት ዉስጥ ከየካቲት 01 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ተሰናበቱበት ጊዜ ድረስ ከአራት ዓመታት በላይ በተለያዩ የተጠሪ ድርጅት ዉስጥ ሲያገለግሉ የቆዩ መሆኑን የተጠሪ ጅርጅት በማያዉቀዉ ምክንያት ከስራ ገበታቸዉ ላይ

ከጠፉበት ከጥቅምት 26 ቀን 2014 ዓ.ም አመልካች መሸፈን ያለባቸዉ የስራ መደብ ክፍት ሆኖ የጠበቃቸዉ መሆኑን፤በወቅቱ ችግር ምክንያት የተጠሪ ድርጅት የሚዲያ ቤት በመሆኑ በከፍተኛ ሁኔታ ጥበቃዉ እንዲጠናከር የተባለ ቢሆንም አመልካች ወደ ስራ ገበታቸዉ ይመለሳሉ በሚል ተስፋ በተለያዩ ጊዜ ወደ ስራ ገበታቸዉ እንዲመለሱ ማስታወቂያ እንዲወጣ ተደርጓል፤ሁለት ጊዜ ማስታወቂያ ወጥቶ ያልቀረቡ ስሆን የቤተሰባቸዉን ችግር ግምት ዉስጥ በማስገባት የህደር ወር ደሞዝ ተከፍሏል፤አመልካች በስራ ላይ ባለመገኘታቸዉ የስራ ዉላቸዉ ከታህሳስ 01 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ከስራ እንዲሰናበቱ ተደርጓል፤የአመልካችን የስራ መደብ ክፍት አድርጎ የመጠበቅ ግዴታ የለብንም፤ከጥቅምት 24 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ በእስር ላይ ሰለመቆየታቸዉ በከሳቸዉ ላይ ያቅርቡ እንጂ ይህንን የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረቡም፤በህጉ ከተቀመጠዉ ጊዜ ካለፈ የተጠሪ ድርጅት ከስራ ገበታቸዉ የጠፉትን ሰራተኛ ተቀብሎ ወደ ስራ ለመመለስ ሃፊነት የለበትም፤ላልሰሩት ስራ የአራት ወራት ደሞዝ የሚከፍልበት ምክንያት የለም፤ያልተጠቀሙበት የዓመት እረፍት የ30 ቀን ተኩል ብቻ ነዉ፤ስንብቱ በሕግ አግባብ እና ከበቂ በላይ ማስጠንቂቂያ በመስጠት የተወሰደ አስተዳዳራዊ እርምጃ ሰለሆነ አመልካች ያቀረቡት የተለያዩ ክፍያዎችን ሊንከፈል አይገባም ያቀረቡት ክስም ዉድቅ ይሁን በሚል ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተዉ ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን በቃል አከራክሮ ምስክሮችን ሰምቶ አመልካች ለምን ያህል ጊዜ የታሳሩ ሰለመሆኑ ከፖሊስ ካጣራ በኋላ አመልካች የተሰናበተዉ በህገ ወጥ ነዉ የስንበት ክፍያ ብር 13,522.92(አስራ ሶስት ሺህ አምስት መቶ ሃያ ሁለት ብር ከ 92 ሳንትም)፤የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ የሁለት ወር ደሞዝ ብር 9,362(ዘጠኝ ሺህ ሶስት መቶ ስልሳ ሁለት)፤የካሳ ክፍያ ብር 28,086(ሃያ ስምንት ሺህ ሰማንያ ስድስት)፤የአመት ዕረፍት ብር 4,759(አራት ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ ዘጠኝ) ክፍያ ለዘገየበት ብር 7,021.50(ሰባት ሺህ ሃያ አንድ ብር ከ50 ሳንትም) ተገቢዉ የመንግስት ግበር ቀንሰዉ ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍሉ በመዝገብ ቁጥር 89684 ላይ በ28/08/2014 ዓ.ም ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በዉሳኔዉ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታቸዉን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ስሆን ከፍተኛ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ተጠሪ ማስጠንቀቂያ የመስጠት ግዴታዉን በመወጣት አመልካች በስራቸዉ ላይ ካልተገኙ የስራ ዉሉን ማቋረጡ ህግን መሰረት ያደረገ በመሆኑ የተጠሪ የስራ ዉሉን በማቋረጡ በፊት ማስጠንቀቂያ ከመስጠት በለፈ አመልካች ከስራ የቀረበት ምክንያት በቂ የሆነ ምክንያት ነዉ ወይም በቂ ምክንያት አይደለም በሚል እንዲያጣራ የተጣለበት የህግ ግዴታ ሳይኖር እንዲሁም በቂ የሆነ ምክንያት መኖር አስሪዉ የስራ ዉሉን እንዳያቋርጥ የሚያደርግ ሰለመሆኑ በግልጽ በህጉ ላይ የተደነገገ ነገር ሳይኖር የስር ፍርድ ቤት ከህጉ ይዘት እና አላማ ዉጭ አመልካችን በቂ በሆነ ምክንያት ከስራ ቀርተዉ እያለ ተጠሪ የስራ ዉሉን ማቋረጡ ህግ ወጥ ነዉ ሲል የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ መስጠቱ የግራ ቀኙን ክርክር እና ህጉን መሰረት ያደረገ አይደለም በሚል ለአመልካች የከሳ ክፍያ፤የስራ ስንብት እና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ለአመልካች ተጠሪ ሊከፍል አይገደድም በሚል የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በማሻሻል በመዝገብ ቁጥር 277353 ላይ በ18/12/2014 ዓ.ም ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት የቀረበዉ የሰበር አቤቱታም ከፍ ሰል የተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል አመልካች እንዲታረምላቸዉ ነሃሴ 25 ቀን 2014 ዓም በተጻፈ በማቅረባቸዉ ነዉ፡፡የሰበር አቤቱታቸዉ ይዘትም፡ በስራ ላይ እያለሁ የእኔ አስተዋጽ በለሌበት ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ጋር በተያያዘ ታስሬ የነበረ ሰለመሆኑ በፖሊስ ተረጋግጧል ይህ ሀሰት ሰለመሆኑ ተጠሪ ያቀረበዉ ክርክር የለም፤በታስርኩበት ጊዜ ተጠሪ ደሞዝ ሲከፍለኝ ነበር፤በበቂ ሁኔታ ከስራ መቅረቴ ከተረጋገጠ የስራ ዉሌ ሊቋረጥ አይገባም፤የጥሪ ማስታወቂያ በወጣበት ጊዜ አመልካች የት እንደለዉ እየታወቀ ፤የስራ ዉል ሊቋረጥ የሚገባዉ በአሳመኝ እና ህጋዊ በሆነ ምክንያት መሆን አለበት፤በስራ ገበታየ ላይ ያልተገኘሁት በግዳጅ በመያዜ ነዉ፤ከስራ ዉል መቋረጥ ጋር በተያያዘ የስራ ክርክር የሚያስገኙትን መብትና ጥቅሞች በግልፅ ባይጠየቅም

እንኳን ህጉ በሚፈቅደዉ በችሎቱ መወሰን ነበረበት ስለሆነም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በሚል ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ሰበር አጣሪ ችሎትም የሰበር አቤቱታዉን መርምሮ አመልካች በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በእስር ላይ መሆናቸዉ አዉቆ ደመወዝ ለቤተሰብ መከፈሉ ተረጋግጦ እያለ ይግባኝ ሰሚዉ ፍ/ቤት ያቀረቡት ምክንያት በቂ ነዉ አይደለም የማጣራት ግዴታ የለባቸዉም በማለት የፌዴራል የመጀመሪ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ የሻረበት አግባብነት ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

በዚህ መሰረት ተጠሪ በ12/05/2015 ዓ.ም በተጻፈ መልስ ያቀረቡ ስሆን ይዘቱም፡የስር ፍርድ ቤት ዉሉ የተቋረጠዉ በአግባቡ ነዉ ያለዉ ትክክል ነዉ፤አመልካች በስራ ላይ ባለመገኘታቸዉ ሁለት ጊዜ ማስታወቂያ ወጥቶ ስራዉ ላይ በለመገኘቱ ከስራቸዉ ሊሰናበቱ ችሎኣል፤አመልካች በሰራ ገበታቸዉ ላይ ሊገኙ ያልቻሉበትን ምክንያት ለተጠሪ ያቀረቡት ማስረጃ የለም፤ሰራተኛዉ ከአምስት ቀናት በላይ የቀረ ከሆነ ያለማስጠንቀቂያ ሊያስናብተዉ የሚችል ድርጊት ስለመሆኑ በአሰርና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/11 አንቀጽ 27(1)(ለ) ስር ተመላክቷል፤አመልካች በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መታሰራቸዉን ተጠሪ ያወቀዉ በችሎት ትዕዛዝ ሰሰጥ በቀረበዉ ማሰረጃ ነዉ፤በስር ፍርድ ቤት ያልተደረገ ክርክርን መሰረት በማድረግ የሚሰጥ ዉሳኔ ተገቢነት የሌለዉ ነዉ ሰለሆነም በይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ዉሳኔ በመሆኑ ይጽናልን በሚል ተከራክረዋል፡፡

አመልካች በበኩሉ የሰበር አበቱታቸዉን በማጠናከር የመልስ መልስ ጥር 19 ቀን 2015 ዓ.ም በተጻፈ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከግራ ቀኙ የቀረበዉ ክርክር ከፍ ስል የተገለጸዉን ሲመስል ይህ ፍርድ ቤትም ለሰበር አቤቱታ መሰረት ከሆነዉ ዉሳኔ ከግራ ቀኙ ከቀረበዉ ክርክር ከማስቀረቢያ ጭብጥ ለጉዳዩ አግባብነት ካለዉ የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡እንደመረመርነዉም ምላሽ የሚሻዉ ጭብጥ ጉዳይ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ ፍርድ ቤት ተጠሪ የአመልካችን ስራ ዉል ሲያቋርጥ በህጉ የተደነገገዉን መሰረት ማስጠንቀቂያ በመስጠት ነዉ ሲል የደረሰበት ድምዳሜ ህጉን የተከተለ ነዉ ወይስ አይደለም የሚል ሆኖ ተገኝቷል፡፡አመልካች በስራ ገበታቸዉ ላይ ያልተገኙበት ምክንያት ከጥቅምት 24 ቀን 2014 እስከ ጥር 08 ቀን 2014 ዓ.ም በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ምክንያት በእስር ላይ ነበረኩ በሚል የተከራከሩ ስሆን ተጠሪ ደግሞ ሁለት ጊዜ ማስታወቂያ በማዉጣት አመልካች በሰራ ላይ መገኘት ስላልቻለ የስራ ዉሉን አቋርጫለሁ የሚል ነዉ፡፡ሰራተኛዉ ከ30 ቀን ለማይበልጥ ጊዜ ስታሰር እና መታሰሩን በ10 ቀን ዉስጥ ለአሰሪዉ ሲነገረዉ ወይም ይህንኑ አሰሪወ ማወቅ ሲገበዉ ለስራ ማገድ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 18(3) ሥር ተመላክቷል፡፡ከዚህ ድንጋጌ የሚገዘዉ አሰሪዉ ሠራተኛዉ ከ30 ቀን የማይበልጥ ጊዜ የታሰረ ከሆነ ይህን በ10 ቀን ዉስጥ ለአሰሪዉ ማስወቅ ያለበት እና አሰሪዉም ለአንድ ወር የሰራ መደቡን ክፍት አድርጎ መቆየት ያለበት ሰለመሆኑ ያስገነዝባል፡፡የዚህ ድንጋጌ ተፈጻሚነት ሰራተኛዉ ከ30 ቀናት ለማይበልጥ ጊዜ የታሰራ ከሆነ እና ይህንንም በ10 ቀን ዉስጥ ለአሰሪዉ ካሳወቀ ነዉ፡፡ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመጣ አመልካች በእስር ላይ የነበሩት ከጥቅምት 24 ቀን 2014 ዓ.ም እስከ ጥር 8 ቀን 2014 ዓ.ም ነዉ፡፡የተሰሩትም 2 ወር ከ14 ቀናት ስሆን በህጉ ከተቀመጠዉ ቀናት በላይ መተሳረቸዉን ነዉ፡፡ለዚህን ያህል ጊዜ ህጉ ከሚፈቀደዉ ቀን በላይ ሰራተኛዉ ታስሮ ከተገኘ አሰሪዉ ሰራተኛዉን የሚጠብቅበት ሁኔታ ያለ ሰለመሆኑ በአዋጁ የተደነገገ ነገር የለም፡፡የአሰሪዉ ጥፋት በአዋጁ ከተደነገገዉ ዉጭ የሰራተኛዉን የስራ ዉል አቋርጦ ሲገኝ ነዉ፡፡በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪ ማስታወቂያ ማዉጣቱን በአመልካች በኩል ክዶ የተከራከረዉ ነገር የለም፡፡የተጠሪ ድርግት ከህጉ ዉጭ ነዉ የሚባለዉ የአዋጁን አንቀጽ 18(3) ተላልፎ ከተገኘ ነዉ፡፡በአዋጁ አንቀጽ 27(1ለ) በዚህ አዋጅ ከተመለከቱ ዕረፍቶች እና ልዩ ልዩ ፈቃዶች ዉጭ የፁሑፍ ማስጠንቀቂያ በስድስት ወር ዉስጥ ለአምስት ቀናት ከስራ መቅረት የስራ ዉል ለማቋረጥ ምክንያት እንደሚሆን ይደነግጋል፡፡ለተከታታይ አምስት የስራ ቀናት ከሰራ መቅረት የስራ ዉልም ለማቋረጥ ምክንያት መሆኑን ከድንጋጌዉ የሚንገነዘበዉ ጉዳይ ነዉ፡፡አመልካችም በእስር የቆዩበትም ከህጉ ከተደነገገዉ ቀን ባለይ ነዉ ይህ

ከሆነ ደግሞ በተጠሪ የተወሰደዉ እርምጃ ህጉን የተከተለ ነዉ ከሚባል በቀር ህገ ወጥ ነዉ የሚያስብል ሆኖ አላገኘነም ስለሆነም በይግባኝ ጉዳዩን የተመለከተዉ ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት አይቻልም፡፡

ሲጠቃለል በስር ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠዉ ፍርድ የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘንም፡፡በመሆኑ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

ዉሳኔ

1.የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 89684 ላይ በ28/08/2014 ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 277353 ላይ በ18/12/2014 ዓ.ም የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ በማሻሻል የወሰነዉ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡

2.በዚህ ችሎት ለተደረገዉ ክርክር ላስከተለዉ ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

3.በዚህ ችሎት የተሰጠዉ ዉሳኔ ግልባጭ የስር ፍርድ ቤት ይድረስ፡፡

**ጉዳዩ ዉሳኔ ሰለ አገኘ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም